ኩባንያችን መስፍን ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኃላ.የተወ.የግል ማህበር (FSWE ኢንድስትሪ) ከታች በሰንጠረዡ የተገለፁትን የተለያዩ መጠን ያላቸው የፋብሪካ ግብኣቶች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ስለሚፈልግ

- የተለቀቀበት ቀን: ሰሉስ ታሕሳስ 28, 2018 (ከ 11 ወር)
- መዝግያ ቀን: ጥሪ 13, 2018 4:00 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:100000
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:200
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ጥሪ 13, 2018 4:30 ጥዋት
- ምድብ: ኮንስትራክሽን ማሽነሪን ኣቁሑትን/ ኤሌክትሮ-መካኒክስ ኣቁሑትን ግልጋሎትን/

የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

ኩባንያችን መስፍን ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኃላ.የተወ.የግል ማህበር (FSWE ኢንድስትሪ) ከታች በሰንጠረዡ የተገለፁትን የተለያዩ መጠን ያላቸው የፋብሪካ ግብኣቶች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ስለሚፈልግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች እንድትሳተፉ ድርጅታችን ይጋብዛል::

በጨረታ የሚገዙ ግብኣቶች ዝርዝር

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት ዝርዝር	መለኪታ	ብዛት	ማብራርያ
01	Welding Wire 1.2mm	Roll	400	1 Roll 15kg
02	Steel Cable Ø12mm	M	6300	
03	Self Screw Drill 5.5*55mm	Pcs	12,226	
04	Nut with Washer Gal, M24 *3	Pcs	2,300	
05	Washer, Galvanized M20	Pcs	450	
06	Paint, White Eurotrucker	Liter	2,600	
07	Paint,antirust Gray	Liter	600	
08	Paint,blush Green acc. RAL 5021	Liter	600	Trans Eth, Color
09	Thinner UN 1263	Liter	2,400	
10	Chain Ø13mm,L=7000mm	Pcs	82	

የጨረታው መስፈርት

1. ተጫራቾች በዘርፉ የ2018 ዓ/ም የ o የንግድ ፈቃድ ያላቸው ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የህዳር ወር ቫት ማሳወቅያ ሰነድ ፎቶ ኮፒ በማያያዝ ከጨረታው ዝርዝር(ሰነድ) ጋር ማስገባት ይኖርባቸዋል::

2. ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የህዳር ወር ቫት ማሳወቅያ የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ሰነድ እና የሚመለስ ኦርጅናል በመያዝ የጨረታ ሰነድ ከ 07/01/2026 እ.ኤ.አ ጀምሮ እስከ 21/01/2026 እ.ኤ.አ መቐለ ላጪ ቅርንጫፍ FSWE ኢንድስትሪ በስራ ሰኣት የማይመለስ 200 ብር(ሁለት መቶ ብር) በመክፈል እና ለናሙና የቀረበ ንብረት በማየት የጨረታ ሰነድ መውሰድ ይኖርባቸዋል::

3. ተጫራቶች የተሟላ የጨረታ ሰነድ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን መቐለ ላጪ ቅርንጫፍ FSWE ኢንድስትሪ ጨረታ ከወጣበት ቀን ጀሚሮ እስከ 21/01/2026 እ.ኤ.አ ከጥዋቱ 4:00 ሰዓት ማስገባት ኣለባችው::

4. ጨረታው በ21/01/2026 እ.ኤ.አ ከጥዋቱ 4:00 ሰዓት ተዘግቶ በተመሳሳይ ቀን 4:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት መቐለ ላጪ ቅርንጫፍ FSWE ኢንድስትሪ ቢሮ የሚከፈት ሲሆን ሰነዳቸው የተሟላ ከሆነ ባይገኙም የጨረታ ሰነዱ ይከፈታል::

5. ተጫራቾች የሚያስገቡት ዋጋ ቫት(VAT) ጨምሮ መጥቀስ አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን ያስገቡት ዋጋ ቫት እንደሚያካትት ተቆጥሮ ይወሰዳል::

6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ ክፍያ ማዘዣ (ሲፒኦ) ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በታሸገ ፖስታ ከጨረታው ጋር ማስገባት አለባቸው::በፖስታ ያልታሸገ ሲፒኦ ተቀባይነት የለውም::

7. አሸናፊ ተጫራቾች ጨረታውን ማሸነፋቸው የግዥ ማዘዣ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ ያቀረቡትን ናሙና ተቀባይነት ካገኘ በኋላ በ5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጠቅላላ ዋጋ ቫት ጨምሮ 10% የውል ማስከበርያ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) በማሰራት ከኩባንያችን ጋር ውል መፈራረም አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን ለጨረታ ማስከበርያ ያስያዙት ብር ለድርጅቱ ገቢ ሆኖ ድርጅቱ ሌላ አማራጭ ይወስዳል::

8. አሸናፊ ተጫራቾች ጨረታውን አሸንፈው ውል ካሰሩበት ቀን ጀምሮ በ (ኣስራ) ተከታታይ ቀናት ውስጥ እቃው ማስረከብ አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን ለውል ማስከበርያ ያስያዙት ብር ለድርጅቱ ገቢ ሆኖ ድርጅቱ ሌላ አማራጭ ይወስዳል::

9. ተጫራቾች በሌላ ተጫራቾች ዋጋ ተመስርተው ዋጋ ማስገባት አይፈቀድም፤ እንዲሁም በቅድመ ሁኔታ የተመሰረተ ዋጋ ተቀባይነት የለውም፤ በተጨማሪም ስርዝ ድልዝ እና የተጫራቶች የስልት ስህተት ያለበት የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም::

10. ተጫራቾች ይህን ጨረታ ካሸነፉ ለሌላ ሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት አይችሉም::

11. ተጫራቾች ተጫርተው ያሸነፉት እቃ መቐለ ዋና መስርያ ቤት ድረስ መጥተው ማስረከብ አለባቸው:: ክፍያ በተመለከተ ያቀረቡት እቃ ድርጅታችን ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ተፈትሾ ተቀባይነት ካገኘ በኃላ በ7 ቀናት ውስጥ የሚፈፀም ይሆናል::

12. ኩባንያው የተሻለ አማራጭ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው::

ለበለጠ መረጃ

መስፍን ብረታብረት እና ኢንጂነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር

ስልክ-+251-914726541 መደወል ይችላሉ

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle